# „መናድ“ የሚለው ቃል በዶ/ር ነገደና በአቶ መለስ በተግባር ሲፈተን

„መናድ“ የሚለው ቃል „ና“ ላልቶና ጠብቆ ሲነበብ የተለያየ ትርጉም አለው። ጠብቆ ሲነበብ፤ ተደራጊነትን ሲያመለክት፤ ላልቶ ሲነበብ ደግሞ አድራጊነትን ያመለክታል። ለምሳሌ በቅርቡ ዶ/ር ነገደ „መናድ ያለበት ሕገ-መንግሥት... „ ሲሉ የተጠቀሙበት „መናድ“ ን „ና“ ን አጥብቆ በማንበብ ነው። እሱን በኢትዮሚዲያ፤ በኤካዴፍ እንዲሁም ሌሎች ድህረ-ገጾች ላይ የወጣ ስለሆነ በዚያ ለይ ማንበብ ነው። አቶ መለስ ደግሞ አላልቶ በማንበብ እንዴት እንደተጠቀሙበት እንይ፡፡

በየጊዜው በሚደረጉ ውይይቶችና በሚዲያ በሚወጡ ጽሁፎች ተደጋግሞ የሚሰማውን *„እንደ መለስ ወያኔ ቢሆን ኖሮ ኢትዮጵያ እስከ ዛሬ ትበታተን ነበር፤ ሕዝቡ እምቢ በሎ ነው እንጂ፤“* የሚለው አነጋገር አቶ መለስን ሲያበሳጫቸው ቆይቷል። አሁን በቅርቡ ደግሞ፤ ዶ/ር ነገደ ጎበዜ „መናድ ያለበት ሕገ-መንግሥት“ በሚል ያወጡት ጽሁፍ ከፍተኛ ፋከራ መሰል አነጋገር ሲታከልበት፤ አሁንስ በዛ ምን ባደርግ ነው ይህንን ነገር አደብ የማሲዘው ብለው ይመክሩና የሚከተለውን እርምጃ ይወስዳሉ፤

እሳቸውም እንደ ዶ/ረ ነገደ „መናድ“ ያለበት ሕገመንግሥት ብለው የነሱና ሕገመንገውቱን ሲዳስሱ፤ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 39 ቁጥር 1 እና ቁጥር 4 „ሀ“ እና „ለ“ እፊታቸው ድቅን ይልባቸዋል (ይልላቸዋል?)።አቤ „<<ይሁን>> ይበሉ እርስዎ ይሁን ሲሉ የማይሆን የለምና!!“ እንዳለው፤ ይህንኑ ችሎታቸውን በመጠቀም፤ የአንድ ክልል ምክር ቤት በአንቀጽ 39 ቁጥር 4 ሀ መሰረት በሁለት ሶስተኛ የድምጽ ብልጫ ድጋፍ የተደገፈ የመገንጠል ጥያቄ እንዲያቀርብ ያስደርጋሉ፤ ቁጥር 4 „ለ“ „የፌዴራል መንግሥት የብሔር የብሔረሰቡ ወይም የሕዝቡ ምክር ቤት ውሳኔ በደረሰው በሶስት ዓመት ጊዜ ውስጥ ለጠያቂው ብሔር፤ ብሔረሰብ ወይም ሕዝብ ሕዝበ ውሳኔ...“ እንዲያደራጅ ያዛል።

የማመልከቻውን መግባት ተከትሎ ግን አንድ አስደንጋጭ ነው የሚባል ነገር ይፈጠራል (እንዲፈጠር ይደረጋል)። ጥያቄውን ያቀረበው ክልል ሕዝብ „ለምንድነው ሶስት ዓመት የምንጠብቀው አሁኑኑ ሕዝበ ድምጹ መካሄድ አለበት“ በሚል መፈክር ሰላማዊ ሰልፍ ለመውጣት ጥያቄ ያቃርባል። አሁንም „<<ይሁን>> ይበሉ እርስዎ ይሁን ሲሉ የማይሆን የለምና!!“ እንዳለው፤ ሰልፉ እንዲካሄድ ይፈቀዳል፤ ለአፈጻጸሙ ዶ/ር ነገደ ከላይ በተጠቀሰው ጽሁፋቸው „... በአንድ የትግራይን ሕዝብ በማይወክል ለአናሳ ክሊክ ሙሉ ቁጥጥር ስር ብሄሮቻችንን እንወክላለን እያሉ የሚቀጥፉና ለዚህ ክሊክ ተንበርክከው ብሔሮቻቸውንም ባንበርከኩና ባዋረዱ የወያኔ ቅምጥ ድርጅቶች...“ እያሉ የሚያጣጥሏቸው፤ ድርጅቶች ይህንን ሃላፊነት ተረክበው እነደዝረት ይሾራሉ። ዶ/ር ነገደ ምናልባት ይህንን ትልቅ ሃላፊነት ሊረከቡ እንደሚችሉ ቀደም ብለው አላሰቡበት ከሆነ፤ ይህንን ጽሁፍ ሲያነቡ ስለቅምጦቹ ያላቸውን አቋም ይመረምሩታል የሚል ተስፋ አለኝ። ግጭቶችም በዚያ ክልል ውስጥ በሚኖሩ የተላያዩ ጎሰዎች መካከል እንዲፈጠር ይደረጋል። ሰልፉ ፈጽሞ በክልሉ ውስጥ ምንም ዓይነት ስራ ለመስራት ወደማይቻልበት ደርጃ ስለደረሰ የተጀመረው ልማት እየተደናቀፈ ነው፤ እየተባለ በየቀኑ የሚዲያ ሽፋን እንዲሰጠው ይፈቅዳሉ፤ ረብሻው እንዲፋፋም ይደረጋል፤ በሌሎች ክልሎችም ጥያቄው እንዲነሳ የሚገፋፉ ካድሬዎች ይሰማራሉ። ሕዝቡ የኛስ ምክር ቤት ለምንድነው መብታችንን የማያስከብርልን እያለ በሰላማዊ ሰልፍና በሌላም በሌላም መንገድ ምክር ቤቱን ይጠይቃል።

ማመልከቻውን ባቀረበው ላይ እንቆይና፤- በክልሉ የሚካሄደው ተቃውሞ ከመካረሩ የተነሳ በክልሉ አስተዳዳሪ ላይ የመግደል ሙከራ እንደተደረገ የሚዘግበው ዜና የመገናኛ አውታሮችን ያጣብባል።

ክቡርነታቸው የተቃውሞው መስፋት ስላሳሰባቸው የግድ ለዚህ ልዩ ለሆነ ችግር ልዩ የሆነ መፍትሄ (for exceptional problem exceptional solution) ያስፈልገዋል እንደሚባለው፣ ከራሳቸው ጋር በሃሳብ ሲናወዙ ቆይተው አንቀጽ 39 ቁጥር 4 ላይ ልዩ አተኩሮ ያደርጋሉ፣ ይህ አንቀጽ ምን እንደሚል ከፍ ብሎ አንብባችሁታል አልደግመውም። ክቡርነታቸው አንቀጹ እንደሚለው የሶስት አመቱን ጊዜ አሳጥሮ ከተፈጠረው ውጥረት መገላገል ይገባል የሚል ውሳኔ ይደርሱና የሚከተለውን መልዕክት ለፓርላማ አባሎች ያስተላልፋሉ፡ „በሚቀጥለው መደበኛ ስብሰባ የሬፈረንደም ማዘጋጃውን ጊዜ የሚያሳጥር ህግ ረቅቆ ስለሚቀርብ፣ የድጋፍ ድምጽ እንድትሰጡ ብቻ ሳይሆን፣ በፓርላማው በሙሉ ድምጽ የተደገፈ መሆኑን ለማስመዝገብ የሁላችሁም መገኘት አስፈላጊ መሆኑን እንድታውቁት፣ ይህንን ለመገንዘብ የተሳነው ዋጋ ይከፍላል“ የሚል መልዕክት ያስተላለፋሉ።

ፓርላማው ተሰበሰበ፣ የሬረንደሙ ማዘጋጃ ጊዜ ወደ 6 ወር ዝቅ ይደረግ የሚለው ረቂቅ ቀረበ። የቀረበውን ህግ ማውጣት አስፈላጊ ያደረገውን ምክንያት ጠ/ሚነሰትሩ በሰፊው ካስረዱ በሁዋላ፣ ይህን የመሰለ አጣዳፊና ትልቅ አስተዋይነትን የሚጠይቅ ሕግ ሲወጣ የመጀመሪያ ጊዜ እንዳልሆነ፣ ሙስና የተበለውን ጠላት ለመዋጋት የወጣውን „የሰየ ሕግ“ እየተባለ የሚጠራውን ሕግ እንደምሳሌ በመጥቀስ ፓርላማው ከተለመደው አሰራር ዝንፍ ሳይል እንዲደግፈው አዝዘው ቁጭ አሉ። የፓርላማው አፈ ጉባዔ ድምጽ አሰጡ በ1 የድምጽ ታአቅቦ ያለምንም ተቃውሞ ሕጉ አለፈ። „ ... እርስዎ ይሁን ሲሉ የማይሆን የለምና!!" እንዳለው እርሳቸው ይሁን አሉ ሆነ!!

ተዚያስ? ተዚያማ እንግዲህ፣ የድምጽ መስጫው ቀን ተወሰነ፣ በክልሉ ከተመዘገቡ ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች ጋር ኮድ ኦፍ ኮንዳክት ተፈረመ። በጊዜው ዋና አጨቃጫቂ ሆነው የተነሱ ጥያቄዎች፣ 1ኛ/ ለሬፈረንደም የሚቀርበው ጥያቄ ምን ይባል? 2ኛ/ የድምጽ አሰጣጡ ዘይቤ እንዴት መሆን አለበት የሚለው ነበሩ። እነዚህን ጥያቄዎች በሚገባ አጥንቶ ሃሳብ እንዲያቀርብ አንድ ኮሚቴ ተቋቋመ። ኮሚቴ ካሁን በፊት በሀገርና ከሀገረ ውጭም በስራ ላይ ውለው አመርቂ ውጤት ያመጡ ሂደቶችን መርምሮ የሚከተለውን ሃሳብ አቀረበ።

ለመጀመሪያው ጥያቄ ካሁን በፊት በጎረቤት አገር ስራ ላይ ውሎ ጥሩ ውጤት ያስገኘው „ባርነት ወይም ነጻነት“ የሚለው ለሬፈርነድም እንዲቀርብ፣ ለሁለተኛው ጥያቄ ደግሞ በኢትዮጵያ በሥራ ላይ ውሎ አጥጋቢ ውጤት ያስገኘው በ2002 ዓ.ም. የሃገራዊና የክልል ምክር ቤቶች ምርጫ የተካሄደበትን ዘይቤ እንዲከተል ሃሳብ፣ እነዚህ ሁለት ሃሳቦች ያለምንም ተአቅቦ የጠ/ሚንስትሩን ይሁንታ ያገኛሉ፣ ሬፈረነደሙ በተመደበለት የ6 ወር ጊዜ ውስጥ ተደረገ። ውጤት „<<ይሁን>> ይበሉ እርስዎ ይሁን ሲሉ የማይሆን የለምና!!“ ሲል በአውራምባ እነደተጻፈው፣ አንቀጽ 39 ቁጥር 4 በትክክል ሥራ ላይ ዋለ። „መናድም“ ሆነ። ተቀዋሚዎች ሕገ-መንግሥቱ ጥሩ ነው፣ ችግሩ አፈጻጸም ላይ ነው እያሉ የሚያሰሙትን ሮሮ ቦታ አሳጣው። ከየትኛውም ወገን ምንም ዓይነት የአፈጻጸም ስህተት ነበረበት የሚል ድምጽ አልተሰማም። እዚህ ላይ ልተዋችሁ ቸር ይግጠመን

አሸብር
ጀርመን

ashebir@t-online.de